**ተረት ተረት / Teret Teret**

ያኔ ወደማታ ከብቶች ሲሰተሩ፣
ለአይን ሲደነግዝ ሰማይና ምድሩ፤
ጋቢያችንን ለብሰን -
ከአፋፉ ቁጭ ብለን ስትል ተረት ተረት፣
እኔም በመጓጓት ብየህ የመሰረት፤
“ከእለታት አንድ ቀን …” እያልህ ስትናገር፣
በጨረቃ ዙሪያ - ያሉትን ከዋክብት - እንመስል ነበር።

ስለአንበሳ ግርማ ስለጅቦች ክፋት፣
ስለነብር ድፍረት ስለጦጣ ብልሃት
ስለበሬ ትዕግስት ስለበግ የዋኃት፣
ስትነግረኝ በተረት፤
ሰማይን ደግፈው የቆሙት ተራሮች፣
እሳት ያነደዱት የመንደር ጎጆወች፣
ጓደኛወች ሆኑን አብረውን ታደሙ፣
በነፋስ ሽውታ ተረት እየሰሙ።

ተረቱን ስትጨርስ እንቆቅልህ አልከኝ፣
ምን አውቅልህ ስልህ ጥያቄ ጠየቅኸኝ፣
መመለስ ቢያቅተኝ ሃገር ስጠኝ አልኸኝ።
ከሰሜን አንስቶ  ሰጠሁህ አድዋን፣
ከደቡብ አንስቼ ሰጠሁህ አዋሳን፣
ከምስራቅ አንስቶ ሰጠሁህ ሐረርን፣
ከምዕራብ አንስቶ ሰጠሁህ ጎንደርን፣
ላሊበላን ብትል -

in the evening when the cattle returned home
when the sky and the earth were brushed by twilight
we sat at the cliff wearing our *gabi*
and you said *teret teret!*
with excitement I said *yemeseret!*
so you spoke *Once up on a time…*
we looked like two stars sitting around the moon

the grandeur of Lion, the treachery of Hyena
the courage of Tiger, the smartness of Ape
the endurance of Ox, the innocence of Sheep
when you told me *teret teret*
nearby mountains that held up the sky
faraway villages that lit small fires
became our friends and joined
listening to the wind that carried your tale

when you finished you said *enkokilishe!*
I said *minawukiish,* so you asked the riddle
I failed to answer
you demanded countries

እሱማ ልቤ ነው ከሆዴ ‘ማይወጣ፣

ለሰጠሁህ ሀገር ይልቅ መልሱን አምጣ፤

በማለት ጠይቄህ ፍቹን ስትናገር፣

ምላሹን ስትነግረኝ ለሰጠሁህ ሃገር፣

በእንቆቅልሽህ ፍች በሳቅ ስንፈራፈር፣

የሚሰሙኝ ሁሉ ይቀኑብኝ ነበር።

ዛሬ በባእድ ምድር፣

ተሰድጀ ስኖር፣

እነሆ በሰማይ ከዋክብት ፈዘዋል፣

ደምቀው አያበሩም በጭስ ተጋርደዋል።

ከስሚንቶ ክምር ከብረት ኳኳታ

ታሪክህ የለውም የሚያርፍበት ቦታ።

ቢሆንም ቢሆንም፣

ልጆን “ተረት ትረት”

ማለቴን አልተውም።

from the North, I picked Adwa

from the South, I picked Awasa

from the East, I picked Harar

from the West, I picked Gondar

you asked for Lalibela

I told you, that’s my heart

it cannot depart from me

I gave you countries,

now give me the answer

as you finished the riddle

I laughed exceedingly

till those who heard me felt jealous.

today I live in the land of others

behold my stars are dim, covered with smoke.

in a pile of cement, among the noise of metals

your story cannot find a place to rest.

And yet still to my son, I say

*teret teret!*